## ኀበ ጢሞቴዎስ ፪ ።

### ምዕራፍ ፩ ።

### ክፍል ፩ ፡ በእንተ ተዘክሮ እኁ ።

፩ እምጳውሎስ ሐዋርያሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ በፈቃደ እግዚአብሔር ወበተስፋ ሕይወት እንተ በኢየሱስ ክርስቶስ ።

፪ ለጢሞቴዎስ ወልድየ ዘአፈቅር ሰላም ለከ ወሣህል ወጸጋ እግዚአብሔር አቡነ ወእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፫ አአኵቶ ለእግዚአብሔር ዘኪያሁ አመልክ በልብ ንጹሕ እምፍጥረትየ ፡ ወዘልፈ እዜክረከ በጸሎትየ መዓልተ ወሌሊተ ።

፬ ወእፈቱ እርአይከ ወእዜክር አንብዐከ ።

፭ ወእትፌሣሕ ተዘኪርየ ሃይማኖተከ ዘአልቦ ኑፋቄ እንተ ኀደረት ላዕለ እምከ ኤውንቄ ወእምሔውትከ ሎይድ ወእፌጽም ፍሥሐየ ወእትአመን ከመ ላዕሌከኒ ።

፮ ወበእንተዝ እዜክረከ ከመ ይትሐደስ ጸጋሁ ለእግዚአብሔር ዘረከብከ በሢመተ እዴየ ላዕሌከ ።

፯ እስመ አኮ መንፈሰ ፍርሀት ዘወሀበነ እግዚአብሔር ዘእንበለ መንፈሰ ኃይል ወንጽሕ ወተፋቅሮ ወጥበብ።

፰ ወኢትኅፈር እንከ በእንተ ስምዑ ለእግዚእነ ወኢታስተኀፍረኒ ኪያየ ሙቁሐ ዳእሙ ፃሙ ለምህሮ በኃይለ እግዚአብሔር ዘአድኃነነ ወጸውዓነ በጽዋዔሁ ቅዱስ ።

፱ ወአኮ በከመ ምግባሪነ ዳእሙ በከመ ፈቃዱ ወጸጋሁ ዘተውህበ ለነ በኢየሱስ ክርስቶስ እምቅድመ ዓለም ።

፲ ወአስተርአየ ይእዜ በምጽአቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ መድኃኒነ ዘሰዐሮ ለሞት ወአብርሃ ለሕይወት ወአሰሰለ ሙስና በትምህርተ ወንጌሉ ።

፲፩ ዘሎቱ ተሠየምኩ ሐዋርያ ወዐዋዴ ወመምህረ ለአሕዛብ ።

፲፪ ወበእንቲአሁ አሐምም ወኢይትኀፈር እምዘ አነ በቱ እስመ አአምር ዘተአመንኩ ወእትአመንኒ ከመ ይክል ዐቂበ ሊተ ዘአማኅፀነኒ እስከ ይእቲ ዕለት ።

፲፫ ወይኩን ለከ አርአያ ውእቱ ቃለ ሕይወት ዘሰማዕከ በኀቤየ በሃይማኖት ወበፍቅረ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፲፬ ዕቀብ ማኅፀንተከ ሠናየ በመንፈስ ቅዱስ ዘኅዱር ላዕሌከ ።

## ወደ ጢሞቴዎስ ፪ ።

### ምዕራፍ ፩ ።

### ክፍል ፩ ፡ ወንድምን ስለ ማስታወስ ።

በእግዚአብሔር ፈቃድ በኢየሱስ ክርስቶስ በምትገኘው በሕይወት አለኝታ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ ። ዮሐ፡ ፩ ፬ ፤ ፩ ዮሐ፡ ፲፩ ፲፫ ። ፩

ለምወድህ ልጄ ለጢሞቴዎስ ! ትድረስ ሰላም ለአንተ ይሁን ያባታችን የእግዚአብሔር ይቅርታ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ይደረግልህ ። ፩ ጢሞ፡ ፩ ፪። ፪

ከተወለድኩ ጀምሮ በንጹሕ ልብ እሱን የማመልከው እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ በቀንም በሌሊትም በምጸልየው ጸሎት ዘወትር አስብሀለሁ። ግ፡ ሐ፡ ፳፫ ፩ ፤ ፳፬ - ፲፮ ፤ ሮሜ ፩ ፰ - ፱ ። ፫

ዕንባህን አስቤ ላይህ እወዳለሁ ። ፬

በእናትህ በኤውንቄና በአያትህ በሎይድ ላይ ያደረችውን ጥርጥር የሌለበት ሃይማኖትህን አስቤ ደስ ይለኛል ፡ ባንተም ፀንታ እንዳለች ተማምኜ ደስታዬን እፈጽማለሁ ። ግብ፡ ሐዋ፡ ፲፮ ፩ ። ፭

ስለዚህም በአንብሮተ እድ በሾምኩህ ሹመት ምክንያት ያገኘኸው የእግዚአብሔር ጸጋ ይታደስ ዘንድ አስብሀለሁ ። ፩ ተሰ፡ ፭ ፲፱ ፤ ፩ ጢሞ፡ ፬ ፲፬ ። ፮

እግዚአብሔር የመፍራትን መንፈስ የሰጠን አይደለምና የኃይል የንጽሕና የፍቅር የጥበብ ነው እንጂ። ሚክ፡ ፫ ፰ ፤ ሉቃ፡ ፳፬ ፵፱ ፤ ሮሜ ፰ ፲፭ ። ፯

እንግዲህ ለጌታችን ስለ መመስከር አትፈር የታሠርኩለትን እኔንም አታሳፍረኝ በዳነንና በልዩ አጠራር በጠራን በእግዚአብሔር ኃይል ለማስተማር ድከም እንጂ ። ሮሜ ፩ ፲፮ ። ፰

የጠራንም እንደ ሥራችን አይደለም ፡ ዓለም ሳይፈጠር በኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰጠን እንደ ቸርነቱና እንደ ፈቃዱ ነው እንጂ ። ፱

ሞትን በሻረው ሕይወትን በገለጣት በወንጌል ትምህርት ጥፋትን በአራቀ በኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት ዛሬ የተገለጠ ። ሮሜ ፲፮ ፳፭ ፤ ፪ ቆሮ፡ ፲፭ ፶፭ ። ፲

ለአሕዛብ መምህር ያዋጅ ነጋሪ ሐዋርያ ሆኜ የተሾምኩለት ። ፩ ጢሞ፡ ፪ ፯ ። ፲፩

ስለ እርሱ መከራዬም እቀበልለት ከለሁበት መከራ የተነሣ አላፍርም ያመንኩትን ዐውቃለሁና እስከዚያችም ቀን ድረስ ያስጠበቀኝም ሊጠብቅልኝ እንደ ሚችል አምናለሁና ። ምዕ፡ ፬ ፰ ። ፲፪

በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅርና በሃይማኖት ፀንተህ ከእኔ ዘንድ የሰማኸው ያ የሕይወት ቃል አብነት ይሁንህ ። ፲፫

ባንተ ላይ በደረው በመንፈስ ቅዱስ በጎ አደራህን ጠብቅ ። ፩ ጢሞ፡ ፮ ፳ ። ፲፬

፳፩ አስተፋጥን ትምጻእ ኀቤየ እምቅድመ ክረምት ፡ ይኤ
ምኑከ ኤውግሎስ ወጱዴስ ወሊኖስ ወቀላውድያ
ወኵሎሙ አኀዊነ ፡፡
፳፪ ወእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ የሀሉ ምስለ መንፈስከ
ወጸጋሁ ምስሌከ አሜን ፡፡

ተፈጸመት መልእክት ካልእት ኀበ ጢሞቴዎስ ወተጽ
ሕፈት በሮሜ ወተፈነወት በእደ አንክሮሎስ ፡፡
ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን ፡፡



ክረምት ሳይገባ ፈጥነህ ና ፡ ኤውግሎስ ጱዴስ ሊኖስ ፳፩
ቀላውድያ ወንድሞቻችን ሁሉ ቸር አለን ይሉሃል ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአሳብህ ጋር ይሁን ፳፪
ጸጋው ካንተ ጋር ይሁን አሜን ፡፡ ቲቶ ፫ ፲፭ ፡፡

ወደ ጢሞቴዎስ የተላከች ሁለተኛይቱ መልእክት
ተፈጸመች ፡፡
ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን ፡ አሜን ፡፡